# በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔርን በማወቅ እደግ

# መግቢያ

ህይወት ጉዞ ነው። እግዚአብሔር ይወድሀል፤በዚህ በህይወት ጉዞ ውስጥ ስኬታማ እንድትሆን ይፈልጋል።ስኬት አንተን ጨምሮ በማንኛውም ሰው ህይወት ውስጥ አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወትህ በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም ይወሰናል።በመረጥከው መንገድ ላይ በመሆን፤በዘለዓለማዊ መንግስቱ ውስጥ የተትረፈረፈውን በረከት እየተካፈልክ ልትፈጽም ትችላለህ ወይም በአንጻሩ ማለቂያ በሌለው ቅዠት ውስጥ ትኖራለህ።ብሩህ የሆነውን መንገድ መርጠህ የእግዚአብሔርን ዓላማ ትፈጽም ዘንድ በየዕለት ህይወትህ እግዚአብሔርን በማወቅ ማደግ ይኖርብሀል።ለዚህ ነው ይህ የመማሪያ መጽሐፍ አንተን ለመርዳት የተዘጋጀው።

እያንዳንዱ ሦስት የትምህርት ክፍሎች አሉት: {1}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤ {2}መሠረታዊ ጥያቄዎች፤እና {3}የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማወቅ እንድታድግ ይረዱሀል።መሠረታዊ ጥያቄዎች ደግሞ በምታውቀው የእግዚአብሔር ቃል እውነት እንድትኖር ይረዳሀል።የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስታወሻ የቃሉን እውነት በልብህ እንድትሰውር ይረዳሀል።

ይህ የመማሪያ መጽሐፍ የችግርህን ምንጭ ወይም ሥር በማወቅ ጠንክረህ እንድታድግ ይረዳሀል፤ጠላትህ ማን ነው፤እንዴትስ ትዋጋዋለህ፤የችግርዎ መፍትሔስ ምንድ ነው የሚሉትን በሚገባ ይመልስልሀል። እግዚአብሔርን በማወቅ እና በህይወትህ የሱን ዓላማ እንዴት መፈጸም እንደምትችል በማወቅ ታድጋለህ።

እያንዳንዱን ትምህርት በጸሎት ጀምር።መልሶቹን በራስህ አገላለጽ ጻፋቸው።በተገለጠልህ እውነት በሚገባ ትመላለስ እና ትኖር ዘንድ  እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ። እግዚአብሔር እሱን በማወቅ ይባርክህ።

# ትምህርት 1

## ችግር
## *(ሐጢያት)*

***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤*** *ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ጻፏቸው።*

1. ሐጢያት ምንድ ነው? 1 ዮሐ 3:4, ያዕቆብ 4:17, ሮሜ 14:23b*

2. እንደ ማቴ 15:19 አገላለጽ፤ሐጢያት ከየት ይመጣል?

3. ሐጢያት ምን ይወልዳል? ያዕ 1:14-17,ሮሜ 6:23

4. ሐጢያት ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ግንኙነት ምን ይፈጥራል? ኢሳ 59:2

5. የሐጢያት ተጠቂ ማን ነው? ሮሜ 3:23

6. በሐጢያት ህይወት ውስጥ ለማይኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር ምን ያደርግላቸዋል? ምሳ 10:29

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።*

1. ሐጢያት እንደሰራህ አውቀሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ትገባ ዘንድ እግዚአብሔር ሐጢያትህን እንዲያሳይህ ይጠቅ።

2. ሐጢያት እንዲሰሩ ምክንያት የሚሆኑ በልብዎ ውስጥ ያሉ አንዳንድ አመለካከቶች ምንድ ናቸው?

3. ሐጢያት እንዲሰሩ ምክንያት የሚሆኑ ችግሮች ምንድ ናቸው?

4. የእግዚአብሔር ቃል፤መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሐጢያትህ የሚናገረውን ለማድረግ ዝግጁ ነህን?
አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር አሁን የንስሀ ልብ እንዲሰጥህ ጸልይ።

**ማስታወሻ:** <u>**ሮሜ 3:23**</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

* ሀ = የጥቅሱ የመጀመሪያው ክፍል
ለ = የጥቅሱ ሁለተኛው ክፍል

ሐጢያት የማንኛውም
ችግር መንስሔ ነው



# ትምህርት 2

## መፍትሔ
## *(ደህንነት)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማስላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።

1. እግዚአብሔር በሐጢያታችን ምክንያት ምን አደረገ? ሮሜ 5:8

2. እግዚአብሔር አንድያ ልጁን፤ኢየሱስን ለእኛ ይሞት ዘንድ ለምን ላከው? ዮሐ 3:16

3. ኢየሱስ ስለ ሐጢያታችን በሞተ ጊዜ ምንን ሰጠን? ኤፌ 1:7

4. እግዚአብሔር ስለ ሐጢያት ይቅርታ ሌላ ለሰው ያቀረበው መንገድ አለን? ሐዋ 4:12

5. ከእግዚአብሔር የሐጢያት ይቅርታን ለመቀበል ማድረግ ያለብን ምንድ ነው? ሐዋ 3:19

6. ከንስሀ ሌላ፤አንድ ሰው በህይወቱ ይለወጥ ዘንድ ማድረግ የሚኖርበት ሁለት ነገሮች ምንድ ናቸው? ሮሜ10:9-10

7. እሱ ጌታችን ከሆነ፤ፈቃደኛ በመሆን እንፈጽመው ዘንድ የሚገባን ኢየሱስ የተናገረን ነገር ምንድ ነው? ሉቃ 14:26, 27 እና 33, ማቴ 10:37-39

8. ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችን እና ጌታችን አድርገን ስንቀበል በህይወታችን ያየነው ለውጥ ምንድ ነው? 2 ቆሮ 5:17

9. እግዚአብሔር ለእሱ እንኖር ዘንድ ምን ይሰጠናል? ሉቃ 11:13

10. በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት እንደሆነ ሰው እንዴት እንኖራለን? ገላ 2:20, 5:24-25

11. በመንፈስ እንመላለስ ዘንድ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንዴት እቀበላለን? ሐዋ 1:5, 8; 2:1-4; 4:31

12. የእግዚአብሔርን ደህንነት ከተቀበልን በኂላ "እግዚአብሔርን በማወቅ እናድግ" ዘንድ እና በሐጢያት ላይ ድልን እንድናገኝ ልናደርግ የሚገባን ምንድ ነው? ገላ 5:16-18, 1 ዮሐ 5:1-3, ሮሜ 6:17-18

13. ስለ ሐጢያታችን ንስሐ እንደገባን እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን እና ጌታችን አድርገን መቀበላችንን የሚያሳይ ውጫዊ መገለጫ ምንድ ነው? ሮሜ 6:4,ገላ 3:27

***መሠረታዊ ጥያቄዎች*:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. እግዚአብሔር እንደሚወድህና፤ኢየሱስ ስለ አንተ እንደሞተ፤እንዲሁም በኢየሱስ ብቻ የሐጢያትን ይቅርታ እንደምትቀበል ታምናለህን ? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን እግዚአብሔር የፍቅሩን እና የደህንቱን እውነት እንዲያበራልህ ጸልይ።

2. ስለ ሐጢያትህ ንስሀ ገብተህ፤ልብህን ለኢየሱስ ሰጥተሀልን፤እንዲሁም በግልጽ በምታውቃቸው ሰዎች ፊት ኢየሱስ ጌታህ እና አዳኝህ እንደሆነ መስክረሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, ይህንን ጸሎት አሁን ጸልይ እንዲሁም ለአንድ ሰው ኢየሱስ አዳኝህ እና ጌታህ እንደሆነ መስክር፤

"እግዚአብሔር አባት ሆይ, በኢየሱስ ስላሳየኸኝ ፍቅር አመሰግንሀለሁ፤ታስፈልገኛለህ። እኔ ከሰይጣን እና ከዓለም ተመልሻለሁ፤ልቤን ከፍቼ ስለሐጢያቴ ንስሀ እገባለሁ፤ኢየሱስ ሆይ ስለ ሐጢያቴ እንደሞትክ እና ከሞት እንደተነሳህ አምናለው።ወደ ልቤ ግባ ነፍሴንም አድናት።የህይወቴ ተቆጣጣሪ፤አዳኝ እና ጌታ ሁን።በአንተ እኖር ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ሙላኝ።ጸሎቴን ስለሰማኸኝ አመሰግንሀለሁ፤በኢየሱስ ስም እጸልያለሁ።አሜን”


3. እራስህን፤ህብረትህን፤ዓላማህን፤መሻትህን እና ሀብትህን ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰጥሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን በጸሎት ያለህን ሁሉ ለእግዚአብሔር አስረክብ።ለእሱ አገልግሎት እንዴት ማዋል እንደምትችል ጥበብ እንዲሰጥህ ጠይቅ።

4. በየዕለት ህይወትህ ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ትኖር ዘንድ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ይሞላህ ዘንድ ጠይቀህ ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ, አሁን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ይሞላህ ዘንድ እና የሚታዘዝ ልብ እንዲሰጥህ ጠይቅ።

5. የውሐ ጥምቀት በመውሰድ ለኢየሱስ ታዘሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን በተቻለህ ፍጥነት የውኃ ጥምቀት ለመውሰድ ወስን።

**ማስታወሻ:** **<u>ዮሐ 3:16</u>** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

ለእሱ እንኖር አንድ ሁሉንም
ነገር ለእግዚአብሔር
ማስረከብ አለብን



# ትምህርት 3

## ዓላማ
## *(የዘለዓለም ህይወት)*

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።

1. የዘለዓለም ህይወት ምንድ ነው? ዮሐ 17:3

2. እግዚአብሔር ማን ነው? ኢሳ 46:9, መዝ 90.2, ኢሳ 57:15

3. እግዚአብሔር እራሱን ለእኛ እንዴት ገለጠ? ዕብ 1:1-2; ቆላ 1:13-16; ዮሐ 1:1-4,9,14; መዝ 19:1-3

4. ኢየሱስ እግዚአብሔር ነውን? ኢሳ 9:6, ዕብ 1:8, ዮሐ 20:28

5. ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር ራሱን በግለጡን እንዴት ተናገረ? ዮሐ 4:24; 14:16-17; 16:7-11

6. የእግዚአብሔር 13ቱ ባህሪያት ምንድ ናቸው?

   ሀ. ኤር 23:23-24

   ለ. ኢዮብ 42:2

   ሐ. 1 ዮሐ 3:20

   መ. 1 ዮሐ 4:16

   ሠ. 1 ዮሐ 1:5

   ረ. ኢሳ 6:3

   ሰ. መዝ 103:8

   ሸ. 1 ጢሞ 1:17

   ቀ. 2 ጢሞ 2:13

   በ. ዳን 9:14

   ተ. ኢሳ 45:21

   ቸ. ሮሜ 8:33

7. የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሰው ዘር ምንድ ነው? 2 ጴጥ 3:9

8. ለምን እግዚአብሔር ሰዎች ንስሐ እንዲገቡ ይፈልጋል? 1ዮሐ 1:2-3

9. እግዚአብሔር ከእሱ ጋር ህብረት ሲኖርህ በህይወትህ ሊሰራው የሚፈልገው ነገር ምንድ ነው? 2 ጢሞ 1:9

10. የእግዚአብሔርን ዓላማ በህይወታችን ለማወቅ እና ለመፈጸም ምን ማድረግ አለብን?
ፊሊ 2:12-13, ዕብ 5:9

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. እግዚአብሔርን እና የላከውን ልጁን ኢየሱስን ለማወቅ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔርን እሱን ታውቀው ዘንድ ጠይቅ።


2. በእውነት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር የሚናገረውን ታምናለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ስለ አለማመንህ ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እሱን የሚናገረውን ታምን ዘንድ እምነት እንዲሰጥህ ጸልይ።

3. ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት እንዲኖርህ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር።

4. በህይወትህ የእግዚአብሔርን ዓላማ በሙሉ ልብህ ለማወቅ እና ለመፈጸም ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ያንን ለማድረግ ወስን።

5. ክርስቶስ እንዳዘዘህ በመታዘዝ ህይወት ውስጥ ለመኖር ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤እግዚአብሔር የሚታዘዝ ልብ እንዲሰጥህ ፀልይ።

**ማስታወሻ**: **ዮሐ 17:3** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።



በህይወታችን የእግዚአብሔርን ዓላማ
ለመፈጸም መኖር አለብን

# ትምህርት 4

## ጠላት
## (መንፈሳዊ ውጊያ)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ፡፡ ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው፡፡

1. ሊያጠፋህ የሚፈልገው ማን ነው? 1 ጴጥ 5:8

2. ሊያጠፋን ከሰይጣንን ጋር የሚሰራው ማን ነው? ኤፌ 6:12

3. ዲያቢሎስ እግዚአብሔርን እንዳንታዘዝ እንዴት ይፈትነናል? ዘፍ 3:1-6,13; ሉቃ 4:1-13; ያዕ 1:14-16

4. እግዚአብሔር እንድንፈተን ለምን ይፈቅዳል? 1 ጴጥ 1:6-7, ሮሜ 5:3-5

5. የሰይጣንን ፈተና ማሸነፍ ትችላለህን? 1 ቆሮ 10:13

6. እግዚአብሔር እናመልጥ ዘንድ የሰጠን መንገድ ምንድ ነው? ማቴ 26:41, ኤፌ 6:10-11

7. ስምንቱ መንፈሳዊ የጦር እቃዎች ምንድ ናቸው? ኤፌ 6:13-18

| | |
|---|---|
| ሀ. | ለ. |
| ሐ. | መ. |
| ሠ. | ረ. |
| ሰ. | ሸ. |

8. የእግዚአብሔር እቃ ጦር ሰይጣንን እንመታ ዘንድ የሚያስችለን እንዴት ነው? 2 ቆሮ 10:3-6

9. ሰይጣንን ለምን እንቃወማን? 1 ዮሐ 4:4

10. አንድ ሰው በፈተና ውስጥ በሚሆንበት ጊዜ ሐጢያትን ተጽዕኖ ለማሸነፍ ማድረግ ያለበት አራት ነገሮች ምንድ ናቸው? ማር 16:17, ያዕ 5:16, 1 ዮሐ 1:9, ሉቃ 17:3-4, ዘለዋውያን 6:2-5

***መሠረታዊ ጥያቄዎች***: በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. ጠላትህ ሰይጣን እንጂ፤እግዚአብሔር፤ሰዎች ወይም ሁኔታዎች እንዳልሆኑ ታውቃለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤በዚህ ቀን ለመቀበል እና ለማመን ልብህን አዘጋጅ።

2. በከፍተኛ ሁኔታ የምትፈተንባቸው ነገሮች ምንድ ናቸው?


   በምትፈተንባቸው ነገሮች ላይ ድል እንድታገኝ እግዚአብሔር ልብህን እና አዕምሮህን ታጸዳ ዘንድ ጥንካሬ፤ጥበብ እና ጽናት እንዲሰጥህ ጸልይ።

3. በየዕለቱ በሰይጣን ላይ ድልን አግኝተህ ስለመኖር እርግጠኛ መሆንን ለማረጋገጥ መንፈሳዊ የጦር እቃህን ትፈትሻለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር።

4. ማንኛውንም አይነት ሀሳብ እና መሻት በእግዚአብሔር ፈቃድ መስመር ውስጥ ለማስገባት ትፈልጋህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን መፈለገን ጀምር።

5. በአንተና በሌሎች ህይወት ውስጥ ከሐጢያት ለመራቅ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን አድርገሀልን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግን ጀምር።

**ማስታወሻ**: **<u>1 ጴጥ 5:8</u>** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።




**ሁሉንም የእግዚአብሔርን የጦር እቃ መልበስ አለብን**

# ትምህርት 5
# መንፈሳዊ እድገት
# (ለኢየሱስ መኖርን መማር)

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤**ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።

1.ሦስቱ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃዎች ምንድ ናቸው፤በእያንዳንዱ የእድገት ደረጃዎች ምን ይሆናል?
1 ዮሐ 2:12-14

ሀ.

ለ.

ሐ.

2. ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ህብረት ለማሳደግ በየዕለቱ ምን ማድረግ አለብን?
ሉቃ 9:23, ሮሜ 12:1-2

3. እግዚአብሔርን በማወቅ እናድግ እና በእምነታችን ላይ እንጨምር ዘንድ ከልባችን መሻት የሚያስፈልጉን ነገሮች ምንድ ናቸው? 2 ጴጥ 1:5-11

4. በእግዚአብሔር ስናድግ አዕምሯችን ይታደሳል።ምን አይነት ነገሮች ናቸው ከህይወታችን መወገድ ያለባቸው፤ምን አይነት ነገሮች ናቸው በስፍራው መተካት ያለበት።ኤፌ 4:17 - 5:16

| <u>ሊወገዱ የሚገባቸው</u> | <u>ሊተኩ የሚገባቸው</u> |
|---|---|

5. በመንፈሳዊ ህይወታችን እናድግ ዘንድ ከሰዎች ጋር የሚኖረንን ችግር እንዴት እንፈታለን? ማቴ 5:23-24; 18:15-17

6. በመንፈሳዊ ህይወታችን እናድግ ዘንድ እንዴት መኖር አለብን? ሮሜ 8:5-6, ገላ 5:16-25

7. መንፈሳዊ እድገት ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን ህብረት እንዴት ይረዳዎታል?
   ዮሐ 7:17, ኤፌ 5:17

8. ይህንን ህይወት እንለማመድ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚያስችለን ምንድ ነው?
   ሮሜ 8:1, 13-14, 28, 31, 35-39; ቆላ 1:9-13

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡


1. በየትኛው መንፈሳዊ እድገት ደረጃ ውስጥ ነው ያለኸው?

2. በመንፈሳዊ ህይወትህ ታድግ ዘንድ በየቀኑ ህይወትህን ለኢየሱስ ክርስቶስ ታረክበለህን? አዎ__ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ህይወትህን ሁሉ ለክርስቶስ አስረክብ፤በየቀኑ ጠዋት የመጀመሪያውን ነገር ማድረግን ቀጥል፡፡

3. በመንፈሳዊ ህይወትህ ታድግ ዘንድ በእምነትህ ላይ የተጠቀሱትን ነገሮች ልትጨምር ትፈልጋለህን፤በተገቢው ቅደም ተከተል ታርጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ጀምር፤እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

4. በመንፈሳዊ ህይወትህ ታድግ ዘንድ እግዚአብሔር ከህይወትህ እንድታስወግድ የሚፈልጋቸው ምን አይነት ነገሮችን ነው?

   አሁን ንስሀ እየገባህ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮችን ከህይወትህ እንዲያስወግድ ፀልይ በምትኩም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን እንዲተካ ጸልይ፡፡




5. በመንፈስ ትመላለስ ዘንድ ሀሳብህን በመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ላይ ለማድረግ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር ሀሳብህን እና ፈቃድህን በመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ላይ ማድረግ ትችል ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ በህይወት ውስጥ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነገር ነውን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤በህይወት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ቅድሚያ ለመስጠት ወስን፡፡

**ማስታወሻ:** <u>ሉቃ 9:23</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡

ሦስቱ የመንፈሳዊ እድገት ደረጃች

# ትምህርት 6

## መንፈሳዊ ምግብ
## (ጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት)

### ሀ. ጸሎት

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤** ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።

1. ከእግዚአብሔር ጋር ትነጋገር ዘንድ ወደ አስደናቂው የእሱ ህልውና እንዴት ትገባለህ?
   መዝ 100:4, 1ጢሞ 2:8

2. እግዚአብሔርን ማመስገን ምን ለማድረግ ይረዳናል? ኤፌ 5:18-20

3. ሁለቱ የጸሎት መንገዶች ምንድ ናቸው? 1ቆሮ 14:15

4. በመንፈስ እንዴት እጸልያለንን? ሮሜ 8:26, 1 ቆሮ 14:14

5. በመንፈስ የመጸለይ አስፈላጊነት ምንድ ነው? ይሁዳ 20

6. በአዕምሯችን እንዴት እንጸልያለን? ማቴ 6:5-13

5. ከእግዚአብሔር እንድንጸልይ ካስተማረን ነገሮች ጥቂቶቹ ምንድ ናቸው? ማቴ 5:44, 9:38;
   መዝ 32:5-6, 122:6; ያዕ 1:5, 5:16; 1 ጢሞ 2:1-3

6. መጸለይ ያለብን መቼ ነው? 1 ተሰ 5:17, ሉቃ 18:1

7.እንድንጸልይላቸው እግዚአብሔር ያስተማረን ነገሮች ምንድ ናቸው? ማቴ 5፤44, 9፤38,መዝ 32፤5-6,122፤6,ያዕ 1፤5,5፤16,1ኛ 1ጢሞ 2፤1-3

9. ጠላትን ለመምታት በጸሎት ህይወታችን ላይ መጨመር የሚያስፈልገን ምንድ ነው?
   ማቴ 17:21

10.ለኢየሱስ የምንኖር ከሆነ፤ጸሎታችንን አስመልክቶ የሰጠን የተስፋ ቃል ምንድ ነው ?
   1 ዮሐ 3:22; 5:14

11. እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንዳይሰማን የሚያደርጉ ነገሮች ምንድ ናቸው? ያዕ 4:3, መዝ 66:18, 1 ጴጥ 3:7, ማር 11:25-26

12. እንዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ ምን ማድረግ አለብን? 1 ዮሐ 1:9

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።

1. በጸሎት በምስጋና በተሞላ ልብ ወደ እግዚአብሔር ትቀርባለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤በዚህ አከባቢ ችግር ካለብህ፤ጸሎትህን ስትጀምር የምስጋና መዝሙር ለእግዚአብሔር በመዘመር ጀምር።

2. እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላህ ትፈቅድለታለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ፈቃድህን ለእግዚአብሔር በማስገዛት በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞላ ጸልይ።ስለ ስራው ከልብህ እሱን ማመስገን ጀምር።

3. በመንፈስ ቅዱስ በመጸለይ እምነትህን ትገነባለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር።

4. እግዚአብሔር በሰጠህ ምሳሌ መሰረት ትጸልይባቸው ዘንድ በጠየቀህ ነገሮች ላይ ትጸልያለህን? አዎ __ አይደለም__ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን ማድረግ ጀምር።

5. በህይወትህ እግዚአብሔር ለጸሎትህ መልስ እንዳይሰጥ እንቅፋት የሚሆን ነገር በህይወትህ አለን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤አሁን ንስሀ ግባ።

6. በህይወትህ ስለሚያጋጥሙ ሁኔታዎች ልትጸልይ ሁልጊዜ ዝግጁ ነህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤አሁን እግዚአብሔር የጸሎት መንፈስ እንዲሰጥህ ጸልይ።

7. አስቸጋሪ ጊዜያት ሲያጋጥሙህ በችግሮች ላይ ድል ለማግኘት በጾም እና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ትቀርባህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር።

**ማስታወሻ:** 1 ጢሞ 2:8 በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

## ለ. መጽሐፍ ቅዱስ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል**፤ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።

1. ሰው መኖር ያለበት በምንድ ነው? ማቴ 4:4

2. እንደ ኢየሱስ ተከታይነትህ ለማደግ ምን መመገብ አለብን? 1ጴጥ 2:1-3

3. መጽሐፍ ቅዱስን ማመናችንን እንዴት እናውቃለን? 2 ጢሞ 3:16

# ትምህርት 6 (የቀጠለ)

4. መጽሐፍ ቅዱስ በሚለው ከመኖር ቀጥሎ፤በእግዚአብሔር ቃል ልናደርጋቸው የሚገቡን ስድስት ነገሮች? ኤፌ 3:4, 2 ጢሞ 2:15, መዝ 1:1-2; 119:11, 1 ዮሐ 1:1-3, ዕንባቆም 2:2

ሀ. ለ.

ሐ. መ.

ሠ. ረ.

5. መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና እግዚአብሔር እንዴት ይረዳናል? ዮሐ 16:13-14

6. የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ለእምነታችን ምን ጥቅም ይሰጣል? ሮሜ10:17

7. ቃሉን ስናጠና እና ለሌሎች ስናካፍል ጠላትን ለመምታት የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ይረዳናል? ዕብ 4:12

8. በቃሉ የሚኖሩትን አስመልክቶ ኢየሱስ ምን ይላል? ዮሐ 8:31-32

**መሠረታዊ ጥያቄዎች:** በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል፡፡

1. በየዕለቱ መንፈስህን በእግዚአብሔር ቃል ትመግባለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር፡፡

2. የእግዚአብሔር ቃል በህይወትህ የሚየጋጥሙህን ችግሮችን እንዴት እንደምታልፍ የሚሳይህን እና የሚናገርህን እያሰላሰልክ ታስታውሳለህን፤አምሮህን እና ልብህን ታጸዳለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር፡፡


3. የእግዚአብሔር ቃልን በምታጠናበት ጊዜ እና በኋላ ተመልሰህ በልብህ ታሰላስለው ዘንድ ትጽፈዋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር፡፡

4. በምታገኘው አጋጣሚ ሌሎች ይባረኩ ዘንድ እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረህን ነገር ታካፍላለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር፡፡

5. የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍትን እያስታስክ ከታች ጻፋቸው፡፡

**ማስታወሻ:** <u>2 ጢሞ 3:16</u> በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ፡፡

የውስጥ ሰውነታችን እንዲጎለብት በየዕለቱ
የእግዚአብሔርን ቃል እየተበገብን መጸለይ አለብን



# ትምህርት 7

## *መንፈሳዊ እንቅስቃሴ*

## *(ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር ህብረት ማድረግ፤ለሌሎች ስለክርስቶስ መመስከር)*

### *ሀ. ከሌሎች የክርስቶስ ተከታዮች ጋር ህብረት ማድረግ*

***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል***፤*ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።*

1. *ለኢየሱስ እየኖርን ከሆነ ልናደርግ የምንችለው ምንድ ነው?* 1 *ዮሐ* 1:7

2. *ሕብረት ለምን ያስፈልገናል? ዕብ* 10:24-25

3. *እግዚአብሔርን እንደምወድ እንዴት እናውቃለን?* 1 *ዮሐ* 4:20-21; 5:2

4. *እኛ የኢየሱስ እንደሆንን ሌሎች እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? ዮሐ* 13:35

5. *ለሌሎች ክርስቲያን የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዴት እናሳያቸዋለን?* 1 *ዮሐ* 3:17, *ገላ* 6:10, *ያዕ* 1:27, 2:14-17

6. *ሕብረት መፍጠር የሌለብን ከማን ጋር ነው? ምሳ* 12:26, 1 *ቆሮ* 15:33, 2 *ቆሮ* 6:14

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።*

1.*በመንፈሰዊ ህይወት እንድታድግ ይረዱህ ዘንድ ከሌሎች ክርስቲያን የክርስቶስ ተከታዮች ጋር ህብረት ለማድረግ ትፈልጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ዛሬ ጀምር፤እግዚአብሔርም ህብረት እንድታደርግ ወደሚፈልጋቸው ሰዎች እንዲመራህ ጸልይ*

2.*በምትችልበት በማንኛውም ጊዜ ሌሎችን በማገልገል፤በተለይም ክርስቲያን ለሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች የእግዚአብሔን ፍቅር ታሳያለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤በታማኝነት ይህን ለማድረግ ጸልይ።*

3.*ኢየሱስን ከማይወዱ ሰዎች ጋር ህብረት አለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አዎ ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤ክርስቶስን ከሚወዱ ክርስቲያን የሆኑ የክርስቶስ ተከታዮች ጋር ህብረት ማድረግ እና ለእሱ ትኖር ዘንድ እንድትፈልግ እግዚአብሔርን ጠይቅ።*

***ማስታወሻ:*** <u>*ዕብ* l0:24-25</u> *በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።*

## ለ. ስለ ኢየሱስ ለሌሎች መናገር

***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ማሰላሰል፤*** *ጥያቄዎችን ያንብቡ በመቀጠልም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ይመልከቱ። ያሰላስሉ (እግዚአብሔር የሚናገረውን ያስቡ). መልሶቹን በሚያሰላስሉበት ጊዜ በተገለጠልዎ መሠረት በራስዎ አገላለጽ ይጻፏቸው።*

1. እግዚአብሔር ከሰጠን አገልግሎት አንዱ ምንድ ነው? 2 ቆሮ 5:18-19

2. እንደ እግዚአብሔር ሰው እንዴት ማዘጋጀት አለብን? 1ጴጥ 3:15

3. ወደ የዕለት እንቅስቃሴያችን ስታመራ ምን ማድግ አለብን? ማቴ10:7-8

4. የኢየሱስ ምስክር የምሆነው እንዴት እና የት ነው? ሐዋ 1:8

5. ጠፊዋን ዓለም መንፈስ ቅዱስ የሚወቅስበት ሦስት ነገሮች ምንድ ናቸው? ዮሐ 16:7-11

6. ጳውሎስ በተጓዘባቸው ስፍራዎች ያካፍል የነበረው ሁለት ነገሮች ምንድ ናቸው? ሐዋ 20:21

7. ከታች በተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መሠረት ስለ ኢየሱስ መልዕክት ዋና ዋና ነጥቦች ምንድ ናቸው? ሮሜ 3:23; 6:23; 5:8; 2:4; 10:9-10; 6:17-18


8. በኢየሱስ ስም ስንሄድ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ እና የሰጠን የተስፋ ቃል ምንድ ነው? ማቴ 28:18-20

***መሠረታዊ ጥያቄዎች:*** *በሚያሰላስሉበት ጊዜ የተገለጠልዎ ህያው በሆነ እውነት ውስጥ እየኖሩ እግዚአብሔርን በማወቅ እንዲያድጉ ይረዳዎታል።*

1. ወደ የዕለት እንቅስቃሴያችን ስታመራ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሌሎች ተናግረህ ታውቃለህን?
አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤ንስሀ ግባ፤እግዚአብሔር ለሌሎች ምስክር ትሆን ዘንድ እንዲረዳህ ጸልይ።

2. ሌሎች ንስሀ ገብተው ለኢየሱስ ክርስቶስ ይኖሩ ዘንድ ትነግራለህን ወይስ ለሌሎች ወንጌልን ሰብከክ ንስሀ የማስገባት ጉዳይን ሙሉ በሙሉ አስወግደሀል? መንገር __ ማስወገድ__ ያስወገድክ ከሆነ, እግዚአብሔር የጠራውን የኢየሱስ ወንጌል ለሌሎች ትናገር ዘንድ ድፍረት እንዲሰጥህ ጸልይ።

3. ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድገው ወደ ልባቸው ለሚያስገቡ ወገኖች *እግዚአብሔርን እያወቁ እንዴት እንደሚያድጉ* እያስተማርክ ደቀመዛሙርት ታርጋለህን? አዎ __ አይደለም __ መልስዎ አይደለም ከሆነ፤በእነዚህ ትምህርቶች ላይ የተማርከውን ከእነሱ ጋር በመካፈል ጀምር።



***ማስታወሻ:*** **<u>1 ጴጥ 3:15</u>** በማስታወስ የእግዚአብሔርን እውነት በልብዎ ይሰውሩ።

*በመንፈሳዊ ህይወታችን ጠንካራ ለመሆን በየቀኑ የክርስቶስ ምስክር መሆን አለብን*

God has a wonderful purpose for your life. We want to help you find and fulfill that purpose. If you would like further training, prayer, orinformation on how you can work with others to shareabout knowing God where you live; please contact us.

WRITE TO:

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. BOX 633
Grapevine, TX 76099
U.S.A.

Phone (228) 255-9251

by Email
Send your request to basic@basicministries.com
Or
Visit our web site www.basicministries.com

IF YOU WERE BLESSED BY THIS BOOKLET SHARE A COPY WITH SOMEONE. ADDITIONAL COPIES CAN BE DOWNLOADED FROM OUR WEB PAGE www.basicministries.com.

COPIES ARE AVAILABLE IN OTHER LANGUAGES.
CONTACT US FOR MORE INFORMATION.

HAVE YOU EVER WONDERED WHAT LIFE IS ALL ABOUT?

WOULD YOU LIKE TO KNOW GOD?

WOULD YOU LIKE TO KNOW THE SOURCE OF
ALL YOUR PROBLEMS, AND HOW TO OVERCOME THEM?

WOULD YOU LIKE TO KNOW HOW TO
LIVE A CONSISTENT, SUCCESSFUL LIFE?

WOULD YOU LIKE TO SHARE HOW TO LIVE A SUCCESSFUL LIFE
WITH A FRIEND OR FAMILY MEMBER?

!!THEN THIS BOOK IS FOR YOU!!

Compiled by Henry Pulsifer

&

Illustrated by Paula Mingucci

This is one of a series of booklets designed to help you*grow to know God* and fulfill His purpose for your life. Henry has experienced the victory that comes from knowing God for over 60 years; including God's healing from cancer as he walked with the cross. Since his healing he has traveled the world sharing *how to know God;* and helping others find blessings and success by *growing to know Him*, and fulfilling His purpose for their life.

Out of this experience he has compiled several learning guides that enable people to*grow to know God*, and understand how to live the basic Bible principles for blessings and success in life. This particular learning guide is designed to help you *grow to know God* in your personal life by living for Him each day. It can also be used to help you teach others, and is appropriate for individuals or groups.

COPYRIGHT 1990 ALL RIGHTS RESERVED
No part of this booklet may be reproduced without permission from the publisher.
Exception: portions may be reproduced if distributed free of charge.
Proper credit should be given for the source of the material.

PUBLISHED BY:

Brothers & Sisters in Christ

BROTHERS & SISTERS IN CHRIST
P.O. Box 633
Grapevine, TX76099
USA

Phone (228) 255-9251
Email basic@basicministries.com
Web page www.basicministries.com